# ምዕራፍ አንድ

# ሀልወተ እግዚአብሔር

የሃይማኖት መሠረት የሰው ልጅ የሕይወት ጥያቄዎች መልስ የእግዚአብር መኖር ነው እግዚአብሔር በባህርዩ ህልው (ኗሪ) የሆነ ያለ የነበረ የሚኖር ለአኗኗሩ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ህልው (ኗሪ) ነው። ሁሉን ያሆነ፣ የፈጠረ፣ ያደረገ፣ የሠራ በማንም፣ ለምንም፣ ስለምንም ያልሆነ ያልተሠራ ያልተፈጠረ ላለው ለሚኖረው ለነበረው ሁሉ የሕይወት መሠረት የሆነ ያለውን የሚኖረውን ያለፈውን የሚያልፈውን በጊዜው ያሳለፈ የሚያሳልፍ የሚመጣውን የሚያመጣ የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ፣ አስገኚ የሆነ ለእርሱ ግን ለአኗኗሩ ምክንያት የሌለው ህልው አምላክ አለ።

## ስለ ሀልወተ እግዚአብሔር የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ

### ቅዱሳት መጻሕፍት

ከእግዚአብሔር ፊትም ሆነ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ከመገለጡ በኋላ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ሁሉን የፈጠረ ብቻውን የባህርይ አምላክ የሆነ እርሱ ብቻ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ። ለምሳሌ እግዚአብሔር መድኃኒት ነው የሚል ስም ያለው ኢሳይያስ "... እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላ ማንም የለም፣ ከእኔም በቀር አምላክ የለም፣ በፀሐይ መውጫና በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስታጥቅሁህ አንተ ግን አላወቅኸኝም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላ ማንም የለም... ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁስ የተናገርኩስ እኔ

እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክ ነኝና ከእኔ በቀር ሌላ የለምና ወደኔ ዘወር በሉ፣ ትድኑማላችሁ።" በማለት ከእግዚአብሔር ያገኘውን አስተምሮአል። (ኢሳ. 45÷5-7 ቁ. 18-23)።

በተጨማሪም ምዕ 46 ቁ. 9-10፣ 1ኛ ሳሙ. 7÷22፣ 1ኛ ዜና መዋዕ. 17÷20፣ 1ኛ ዜና መዋዕ. 17÷20፣ ዘዳ. 32÷39፣ 1ኛ ቆሮ. 8÷4፣ 1ኛ ጢሞ. 6÷16 ተመሳሳይ መልእክት ያዘሉ ክፍላተ መጻሕፍት ናቸው። እግዚአብሔር የባህርይ አስገኝ ወይንም መነሻና ምክንያት በመሆኑ ሁሉን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ በሁሉ አጥኚነቱ ታዋቂ ሆኖ በተገኘ በሰዎች ልማዳዊ ጥናት በየብስ አጥኚዎች ወይም በጠፈር ተመራማሪዎች ፍለጋ፣ በማይመረመር ወይንም ምክንያት በሌለበት ባህርይ ይኖራል። ከሱ በፊት አምላክ የሌለ ከእርሱም በኋላ የማይሆን ብቻውን አምላክና መድኃኒት መሆኑን በሚከተሉት ጥቅሶች እንማራለን (መዝ. 76(77)÷19፣ ኢሳ. 43÷10-13፣ ኢሳ. 41÷4-5፣ ኢሳ. 44÷6-8፣ ኢሳ. 48÷12-13 ኢሳ. 11÷7-10) ስናነብ ከመለኮታዊ ቃል እንማራለን።

## ህልውናው

እግዚአብሔር እራሱን "እነ ውእቱ ዘሀሎ ወይሄሉ" ያለና የሚኖር እኔ ነኝ (ዘጸ 3÷12) የሚል ራሱን የገለጸ ያለና የነበረ የሚኖር አምላክ እግዚአብሔር ነው። ስሙም ያለና የሚኖር ይባላል (ዘጸ. 6÷2-3፤ ዮሐ. 8÷58፤ ራዕ. 1÷8፤ ዕብ. 13÷8፤ ራእይ 4÷8) ላይ እንደምናነበው ትናንትና ዛሬ ቅድመ ዓለም እና ድኅረ ዓለም ህልው በህላዌሁ የሆነ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው አምላክ መሆኑን መጻሕፍት ያስገነዝቡናል። ቅዱስ ቄርሎስ "ንሕነሰ ንበል ከመ ሕይወት ውእቱ በህላዌሁ - እኛ ግን እርሱ በአኗኗሩ ባሕርያዊ ሕይወት ነው እንላለን" አለ። ቄርሎስ ገጽ 333 ም. 80 ቁ.6።



## ምክንያት የሌለው ህላዌ

ለእግዚአብሔር ህልውና ምክንያት አለመኖሩንና ከእርሱም አስቀድሞ አንዳች አለመኖሩን በባህርዩ ህልው መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ፤ ኤጵፋንዮስ ዘቆጵሮስ በቅዳሴ ገጽ 145 ቁ. 4 ላይ "አልቦ ጥንተ ለህላዌሁ" ለህላዌው (ለአኗኗሩ) መነሻ የለውም ይላል (ርቱዓ ሃይማኖትም) ኢይትአመር ጥንተ ክዋኔሁ የአኗኗኑ መነሻ አይታወቅም። ብሎ ተናገረ ቅዱስ ቄርሎስም "ህላዌሁ ዘኢይትረከብ" ህላዌው የማይመረመር ነው ይላል ቅዳሴ ቄርሎስ 164 ቁ. 3 ስኑቱዩም "ኢተረክበ ሀልወቱ እምኃበ ወኢምንት" "አነዋሩ ከምንም የማይገኝ ነው" ብሎ ተናገረ። ሃ.አበው 504 ክፍል 2-4 ሠለስቱ ምዕትም "አልቦ አመክንዮ ወኢቡዓዴ ለኃበ ዚአሁ ህላዌ አልቦ ዘኮነ መኑሂ ምክንያተ ሕይወቱ እስመ አልቦቱ መዋዕል ለሕይወቱ ወኢይመውት ገሙራ ለሊሁ ፈጣሪ ገባሬ ነፍሳት ወሥጋት - ለሕይወቱ ምክንያት የሆነ ምንም የለም ለሕይወቱ ጊዜያት አይገኙለትም ፈጽሞም ሞት የሌለበት እርሱ ፈጣሪ ነው። የሥጋዎችና ነፍሳትም ሠሪ ነው" ዲዮ ዘአንጾኪያ ገጽ 439 ክፍል 1 ቁ. 6 አለ። ሐዋርያትም "እስመ አልቦ አሥር ለህላዌሁ እንዘ እሳተ መለኮት ውእቱ" ፍችውም እሳተ መለኮት ሆኖ ሳለ (አኗኗሩ) ፍለጋ አሥር የለውም አሉ። ለአኗኗሩ ምክንያት የሌለው ህልው በህላዌሁ ለሆነው አምላክም ዳዊት "መኑ ውእቱ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር መመኑ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእንበለ አምላክነ" ማለት ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማነው ከአምላካችንስ በቀር እግዚአብሔር ማን ነው? ብሎ ዘመረ (ኢሳ. 44÷6-8፤ ም. 48÷12፤ 2ኛ. ሳሙ. 22÷32፤ መዝ. 17÷32፤ 1ኛ ሳሙ. 7÷22፤ ዘዳግ. 4÷32፤ ኤር. 10÷10፤ ኢሳ. 46÷9) እንደተጻፈ በሕላዌው ህልው የሆነ ለህልውናው አንዳች ምክንያት የሌለው ዘሀሎ ወይሄሉ ያለና የነበረ አምላክ ነው።

## ሰዎች ለምን ሀልወተ እግዚአብሔርን ይጠራጠራሉ?

በቀላሉ እንደፍጡር ሊያዩት፣ ሊያገኙት፣ ሊደሰቱበት፣ ሊያነጋግሩት ስላልቻሉ እግዚአብሔር ሁሉን ያስገኘ አምላክ ፍጹምና በዓለም ምሉዕ ሲሆን የማይመረመር ረቂቅ የማይደረስበት ምጡቅ በመሆኑ በመመርመር በማጥናት፣ በመፈላሰፍ፣ በጥናት ሊያውቀው ሊረዳው፣ ሊደርስበት የሚችል የለም። ፍጡር ፈጣሪው ራሱን ካልገለጠለት በቀር በችሎታው ሊያገኘው አይችልም። ምሳሌ ሌላው ፍጥረትም ሊናገረው ሊተረጉመው፣ ይህን ያክላል፣ ይህን ይመስላል፣ መጠኑ፣ ስፋቱ፣ መመርመሩ ልክ አለው ሊል አይችልም። የማይመረመር በመሆኑም በግዘፍ የሚያስቡ በቀላሉ ካላገኙት እንደሌለ ሊገምቱ ይችላሉ "አልቦ ዘረከቦ ወአልቦ ዘይረክቦ አልቦ ዘየአምረከ ወአልቦ ዘይክል ርዕዮተከ ለሊከ ተአምር ርእሰከ" ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቁጥር 5 ሲፈታ "ባህርዩን መርምሮ ያገኘው የሚያገኘውም የለም የሚያውቅህ የለም (በባህርይህ) ሊያይህ የሚችል የለም። ራስህን አንተ ታውቀዋለህ" ማለት ነው።

ሥውር ውእቱ ዘኢይረክብዎ በኀሊና ወምጡቅ ውእቱ ዘኢይጤይቅዎ በልቡና ነዋህ ውእቱ ዘኢይበጽህዎ አንሥርት፤ ቀላይ ውእቱ ዘኢይጸብትዎ ዐሣት። (ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ) እንደተባለ።

ከሁሉ የላቀ፣ የረቀቀ መሆኑ ግልጽ ነው እግዚአብሔር ፈጣሪ ስለሆነ በጥናት በሥጋዊ ስልት በፍልስፍና፣ በምርመራ የሚገኝ አምላክ አይደለም። በፍልስፍና እግዚአብሔርን ቢያገኙት ኑሮ ሃይማኖት ፍልስፍና፣ ፍልስፍናም ሃይማኖት በሆነ ነበር። እግዚአብሔርም ፈጣሪ መሆኑ ቀርቶ በጥናት፣ በፍልስፍና የሚጠና አንድ ረቂቅ ነገር ገና ያልታወቀ ወደፊት የሚደረስበት ፍጡር እንደሆነ በተገመተ ነበር። እግዚአብሔር ግን እውነተኛ ፈጣሪ በመሆኑ ማንም አስቦ ተመራምሮ አይደርስበትም፣ ወደፊትም ማንም በሳይንሳዊ መንገድም አያገኘውም አይደርስበትም፣



እግዚአብሔር በሃይማኖት ብቻ ይታያል፣ በጸሎት ያነጋግራል፣ መልስ ይሰጣል፣ እንደ አምላክነቱ ፍጥረቱን ይመግባል፣ ይጠብቃል። በመሆኑም ስለእርሱ የሚነገረው ትምህርት ሁሉ ሃይማኖት ይባላል። እንግዲያውስ እግዚአብሔር ግሩም ነው። እግዚአብሔር በልብ ብቻ ይረዳል፣ ይታመናል፣ በሃይማኖት ብቻ ይገኛል፣ ይታሰባል እንጂ በጥናት አይገኝም፣ ሥውር ነው። ዮሐንስ "ክንዱ ብከ ዕበይከ ወሥውር ብከ ኃይልከ፤ ለሊከ ብከ አንጦላዕከ ወለሊከ ብከ ተከደንከ" ሲል የማይመረመር፣ የማይገኝ፣ የማይደረስበት መሆኑን አስረድቷል። ቅ.ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቁ. 4። በመሆኑም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያልተማወቀ፣ በጸጋ እግዚአብሔር ያልላቀ፣ በሐሳቡ የወደቀ ሰነፍ "ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር፤ ሰነፍ እግዚአብሔር የለም ይላል" ብሎ ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረ (መዝ. 13፥14)። ቅዱስ ዳዊት በ9ኛው መዝሙርም "ወአልቦ እግዚአብሔር በቅድሜሁ ወርኩስ ኩሉ ፍናዊሁ ... ወይብል በልቡ ኢይትሀወክ ለትውልደ ትውልድ ወኢይረክበኒ እኩይ... ወይብል በልቡ ይረስአኒ እግዚአብሔር ... እስመ ይብል በልቡ ኢይትሐሠሠኒ" እንዳለ በ35ኛው መዝሙርም "ይነብብ ኃጥእ በዘያስሕት ርእሶ ወአልቦ ፍርሐተ እግዚአብሔር ቅድመ አዕይንቲሁ..." እንዳለ ክፉ ሰው የሚሠራውን በደልና ኃጢአት ሁሉ አምላክ እንደሌለና እንደማይፈርድበት እየተሰማው በድፍረት ኃጢአትን ስለሚሠራ ቁጥሩ ሀልወተ እግዚአብሔርን ከካዱ ሰዎች መሆኑን ያስተምረናል እንዲሁም በግዘፍ የሚያስብ ማቴሪያሊስት የሆነው ዓይነ ልቡናው የታወረው ፍጥረት በመንፈሱ ስለማያስተውል አስተሳሰቡም ቀረባቅርብ የሆነ ሰነፍ መሆኑ አዕምሮ የጎደለው ነውና ሀልወተ እግዚአብሔርን ሊጠራጠር ይችላል።

## ሀልወተ እግዚአብሔር የተገለጠባቸው መንገዶች

እግዚአብሔር አለ ይኖራል ያለውንና የነበረውን እግዚአብሔርን የማያምኑትን የምናሳምንባቸው፣ የሚያምኑትንም የምናስተምርባቸው መንገዶች አሉ። ከእነዚህ ለሀልወተ እግዚአብሔር አስረጅ ከሆኑ ነገሮች ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን።

1. ሥነ ፍጥረት፡- ያልሆነ፣ ያልተፈጠረ፣ ያልተሠራ ነገር የለም ማለት ሳይሆን የሆነ ሳይፈጠር የተፈጠረ፣ ሳይሠራ የተሠራ፣ ሳይደረግ የሆነ ነገር የለም። በአንጻሩ የሆነው ነገር ሁሉ አስገኝ አለው። የተፈጠረውም ፈጣሪ አለው፤ የተደረገውም አድራጊ አለው፤ የተገኘውም አስገኝ አለው፤ ስለዚህ ማንኛውም ነገር ያለአስገኝ ሊገኝ እንደማይችል የሚታየውም የማይታየውም ፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ እንዳለው በሥነፍጥረት እንማራለን (መዝ. 18፥1)። በዚህም የፈጣሪን መኖር እንማራለን (ሮሜ 1፥20) "ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትአወቅ በፍጥረቱ በሐልዮ ወበአእምሮ" እንዳለ ሐዋርያው ቅ. ጳውሎስ "ወለእመፈቀድከ ሰማዕተ አማናዊ ተመየጥ ወአልተሀይጽ ኀበ ርዕስከ..."

2. ኅሊና፡- ሰው በተፈጥሮው ረዳት ይሻል፣ ያለረዳት የሚኖር የለም። በላይ ያለ የፈጠረው፣ ያከናወነው ጌታ መኖሩን ኅሊናው ይረዳል። ሕገ-ኅሊና አለው ሲበድል፣ ሲያጠፋ፣ የሚዘልፍ በጎ ሲያደርግ የሚያመሰግን፣ በደስታ የሚሞላ ልዩ ኅሊና በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረ ሰው ሁሉ አለው (1ኛ. ዮሐ. 3፥21፤ ሮሜ. 2፥14-15፤ 1ኛ መቃ. 6፥1-13) "ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘንተ ግብረ ብከመምህር ወሰማዕት እምአፍአ ዘይመርሐከ ለልብከ ኀበ አእምሮተ እግዚአብሔር" ማር ይስሐቅ። ሥነፍጥረትም አእምሮም ኅሊናም የሚያስተምሩት ሀልወተ እግዚአብሔርን ነው።



3. ታሪክ፡- በኅብረ ነቢያት በኩል በብዙ ኅብረ መልክዕ በብዙ ኅብረ ጾታ በብዙ አምሳል ይናገር የነበረ አምላክ በነቢያት ለአበው የተናገረውን ተስፋ በልጁ መገለጥ መፈጸሙ ለኛ ትልቅ መረጃ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ የአምልኮ ሥርዓት ይለያይ እንጂ አምላክን በመፈለግ በልዩ ልዩ አምላክ የዓለም ሕዝቦች በታሪክ ውስጥ መታየታቸው እውነቱን ሁሉም ባያገኙትም ፈጣሪአቸውን ለማግኘት በመድከም ላይ ናቸው። በመድከም ላይ ይገኛሉ (ዕብ. 1፥1-2) ይህም የሰው ባህርይ ከእግዚአብሔር የተገኘ አምላክ እኔ ከሚልበት የፈጣሪነት ክብሩ አክብሮት የሚኖር መሆኑን ነው የሚያመለክተው።

## የእግዚአብሔር ባሕርይ መገለጫዎች

ሀ) እግዚአብሔር ልዑል ክቡር ፍጥረት ሊናገረው ከሚችለው በላይ የሆነ ታላቅነት በመዝሙር፣ በግጥም በቅኔ መልክ ፍጥረት በተሰጥኦው ሊገልጸው የማይችል መንክር ልዑልና ዕፁብ እግዚእና ያለው በብሉይ፣ በሐዲስ ከተናገረው በሊቃውንት ከተተረጎመው በመላእክት ከተነገረው ክብር የበለጠ ሁሉም አድንቆና አመስግኖ ተናግሮና ዘምሮ ሊተረጉመው ከሚችለው በላይ የሆነ ልዑል አምላክ ነው። ይህንንም ቅዱሳን ነቢያት በድንቅ ቃል ምሳሌ የሌለው መልዕልተ ኩሉ የሆነ አምላክ ነው ይላሉ (ኢሳ. 40፥18-26፤ ኢሳ. 66፥1-2፤ ኤር. 23፥24፤ ኤር. 4፥6)።

ለ) ከመለኮታዊት ክሂሎቱ የተነሣ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው። እግዚአብሔር ተስእኖ የሌለበት መለኮታዊ ክሂል፣ ተዋርዶ የሌለበት መለኮታዊ ልዕልና አለው። ከመለኮታዊ ክሂሎቱ በላይ የሆነ የሚሆን አንዳች ነገር የለም። ሁሉም ለሱ ይገዛል በሱ ሆኖአል፣ ተፈጥሮም የዝምታ ዘመንም፣ ጊዜም ዘለዓለማዊነትም፣

ግዘፍም ርቀትም፣ ግኡዝም ነባቢብም፣ የሚታይም የማይታይም፣ ነገር ሁሉ ከእርሱ የተነሣ የሚሆንና የሆነ ነው። ያለድካም መሥራት ያለሕልፈት መኖር (ህልውት) ያለሞት ሕይወት ያለጊዜ መኖር ያለመወሰን ምልዐት ያለመሰልቸት መምራት ያለለውጥ መንግሥት ያለመሰልቸት መያዝ ያለማዘንበል መመልከት የሚቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ተፈጥሮን የሚያዝ የሌለን አምጥቶ የሚያኖር ያለውን የሚያሳልፍ ክሂል (ችሎታ) ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህንንም መለኮታዊ ችሎታ በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ይሰብካሉ፣ ነቢያትም በአንድ መንፈስ ያውጃሉ (ዘፍ- 17፥1፤ ዘፍ. 18፥14፤ ኢዮ. 5፥17፤ ኢዮ. 6፥14፤ ኢዮ. 13፥3፤ ኢዮ. 27፥11-13፣ ኢዮ. 42፥1-2፣ 1-2፣ ኢሳ. 12፥28፤ ኤር. 32፥17፤ መዝ. 138፥1-10፤ ማቴ. 19፥26፤ ሉቃ. 1-33፤ ሉቃ. 18፥27፤ ኤፌ. 4፥6፤ ዮሐ. 1፥3፤ ዳን. 4፥35፤ ዮሐ. 5፥26፤ ራእይ 4፥10-11፤ ራእይ 4፥1-11)።

ሐ) የማይታይ፣ የማይመረመር፣ ረቂቅ አምላክ ነው (ኢዮ. 11፥7፤ ኢዮ. 5፥9-11፤ ኢሳ. 40፥18-28፤ ቈላ. 1፥15፤ 1ኛ ጢሞ. 1፥17፤ ኤር. 23፥24፤ 1ኛ ቆሮ. 13፥12፤ 1ኛ ጢሞ. 1፥17)።

መ) መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ አምላክ ነው እግዚአብሔር ያልነበረበት ወቅት ዘመን ጊዜ ዕለት ቀን ሰዓት የለም አልነበረም፤ የማይኖርበትም ወቅት ዕለት የለም አይኖርም እርሱ ቅድመ ዓለም ድኅረ ዓለም ማዕከለ ዓለም ነበረ። አለ። ይኖራል። ለዘመኑ ጥንት ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም (መዝ.89፥2፤ ኢሳ.43፥1-13 ኢሳ.44፥6፤ ኢሳ.41፥4፤ ኢሳ.48፥12፤ ኢሳ.57፥15፤ ራእይ 4፥1-11፤ መዝ.89፥2፤ መዝ.101፥89 መዝ.144፥12)።



ሠ) መሐሪ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ርኅሩኅ አምላክ ነው። (መዝ. 144፥8-9፤ ማር. 10፥18፤ ሉቃ. 18፥19) በነዚህ ክፍሎች ወሰን የለሽ ቸርነቱን እናነባለን።

*የእግዚአብሔር ምህረት በመጽሐፍ ቅዱስ፤*

ምህረት ማለት ቅጣት ለሚገባው ወንጀለኛ ይቅርታ ርኅራኄ ማድረግ ማለት ነው። (መዝ 50፥1, ቁ.7-8) ለባልንጀራ ለድሀ ምህረት ስናደርግ እግዚአብሔርን እናከብራለን (ምሳ 14፥21 እና 31, ሆሴ 14፥3)

የእግዚአብሔር ልጅ ስለእኛ በመስቀል ላይ በመሞት ለበደለኞች ታላቅ ምህረት አደረገልን (ኤፌ 2፥4-5, 1ኛ ጴጥ 1፥3, ሮሜ 5፥6-10) እግዚአብሔር አምላካችን ከመስዋዕት የበለጠ ምህረትን እንደሚወድ በነቢያት ተገልፆአል። ዛሬ የተነበበውም ወንጌል የሚያስገነዝበንም ይህንኑ ነው። የእግዚአብሔርን ምህረት በብሉይ ኪዳን ስናይ እጅግ የበዛ (ዘኁ 14፥18)፣ እስከ ሰማይ ደመናት የሚደርስ (መዝ 36፥5)፣ እንደሰማይ የረዘመ (መዝ 113፥11)፣ የተትረፈረፈ እና የበዛ (መዝ 36፥7)፣ ቃሉን በሚፈሩት ላይ እስከ ሺህ ትውልድ የሚያፀና (ዘፀ 34፥7)፣ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር (መዝ 113፥17 መዝ 136 በሙሉ) ነው።

በብሉይ ኪዳን ላይ እንደተመለከትነው በብዙ ቦታ የእግዚአብሔር ምህረት ተጠቅሷል። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በመስቀል ላይ በዋለው በልጁ ተገልጧል። ብሉይ ኪዳን በብዙ ገፅ ላይ ከምታስነብበው የምህረት ቃልም በመስቀል ላይ አንድ ቀን የታየው የኢየሱስ ክርስቶስ ምህረት ትርጉም የሰፋ ነው።

እንግዲያውስ እንደ ሎጥ ከእሳት ነጥቆ ያወጣንን የጌታን ምኅረት እናስብ (ዘፍ 19፥19) እንደ ያዕቆብም ከተደረገልን ምሀረትና ርኅራኄ የተነሣ ሳይገባኝ ምህረት በዛልኝ እንበል (ዘፍ 32፥10) እንደ አብርሃምም አሽከር የእግዚአብሔር ምህረት ስለሚደረግልን እንለምን (ዘፍ 34፥12)

እንደ ያዕቆብ ስለተደረገልን ምህረትም እግዚአብሔርን እናመስግን (ዘፍ 24፥27) እንደ ኑኃሚን እግዚአብሔር ተአምራዊ በሆነ መንገድ ስለሚያደርገው ህይወታዊ መስተካከል እግዚአብሔርን እናመስግን (ሩት 2፥20) የእግዚአብሔር ምህረት የእውሮችን ጩኸት ትሰማለች ዕውራንን ታበራለች (ማር 10፥46-52) (ሥርዐተ አምልኮ ገጽ 62)

ረ) ለምልዓተ መለኮቱ ውሳኔ የሌለበት ምሉዕ የሆነ አምላክ ነው። (ኤር. 23፥24፤ 1ኛ ጢሞ 1፥17) ክብር ይግባውና እግዚአብሔር ለምልዐተ መለኮቱ ወሰን የሌለው "ይጸውር ድደ ወይነብር ጠፈረ" የተባለለት ቅዱስ ሕርያቆስ "አኮ ዘበላዕሉ ጠፈር ወዘበታህቱ መሠረት አላቱጠፈር ውእቱ ወመሠረት ውዕቱ" ብሎ የገለጸው ጌታ ምሉዕ ስፉህ ረቂቅ ነው (መዝ. 137፥7፤ ኢዮ 11፥7፤ ማቴ. 5፥35-36፤ 1ኛ ነገሥ 8፥26-28)።

ሰ) በአንድነት በሦስትነት ሲሠለስ ሲቀደስ የሚኖር ቅዱስ አምላክ ነው (ዘፍ 1፥26፤ ዘፍ. 3፥22፤ ዘፍ. 11፥7፤ ኢሳ. 6፥3፤ 33፥22፤ ማቴ. 3፥17፤ ማቴ. 17፥5፤ ዮሐ. 15፥26፤ 2ኛ ቆሮ 13፥14፤ ዕብ. 4፥8)። እግዚአብሔር ስንል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው።

እግዚአብሔር በስም፣ በአካል በግብር ሦስት፣ በመለኮት በአገዛዝ በሥልጣን አንድ አምላክ ነው። ሥላሴ ቅድመ ዓለም አንድነታቸው



ሦስትነታቸውን ሳይጠቀልለው፤ ሦስትነታቸውም አንድነታቸውን ሳይለየው ሳይከፍለው፤ በአንድነት በሦስትነት ነበሩ። በአንድነት በሦስትነት ይኖራሉ "አልቦሙ ጥንት ወኢትፍጻሜት" ጥንትም ፍጻሜም የላቸውም፣ እንዳለ ሃ.አ. "ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ" ሱንትዩስ "ሊሉያን እንበለ ትድምርት ወኅቡራን እንበለ ተሌልዮ" እንዳሉ ሠለስቱ ምዕት።

## ሦስትነታቸው

### በአካል፣ በስም፣ በግብር ሦስትናቸው

1) የአካል ሦስትነት፡- ለአብ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክዕ አለው፤ ለወልድም ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክዕ አለው፤ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክዕ አለው። ይህንንም በተመለከተ የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ አትናቴዎስ "አብኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልክዑ ፍጹም ውእቱ፤ ወልድኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልክዑ ፍጹም ውእቱ፤ ወመንፈስ ቅዱስኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልክዑ ፍጹም ውእቱ" ብሏል። ይህ አካል ግን መጠን፣ ልክ፣ ወሰን የሌለው፤ ምሉዕ፣ ስፉህ፣ ረቂቅ ነው።

2) የስም ሦስትነት፡- አብ የአብ ስም ነው፤ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይጠሩበትም፤ ወልድም የወልድ ስም ነው፣ አብ መንፈስ ቅዱስ አይጠሩበትም፤ መንፈስ ቅዱስም የመንፈስ ቅዱስ ስም ነው፣ አብ ወልድ አይጠሩበትም።

ይህንን አስተምህሮ በተመለከተ አባታችን አግናጥዮስ "አብኒ አብ ውእቱ ኢኮነ ወልደ ወኢመንፈሰ ቅዱሰ ወልድኒ ወልድ ውእቱ ኢኮነ አበ ወኢመንፈሰ ቅዱሰ ወመንፈስ ቅዱስኒ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ ኢኮነ አበ ወኢወልደ"። ሲፈታ "አብ አብ ነው፣ አብ ይባላል እንጂ

ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይደለም (አይሆንም) ወልድም ወልድ ነው፣ ወልድ ይባላል እንጂ አብን መንፈስ ቅዱስን አይሆንም አይባልም፤ መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ አብ ወልድ አይሆንም (አይባልም)" አለ። የአብ ስም የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም መደመሆን፣ የወልድም ስም የአብ የመንፈስ ቅዱስ ስም ወደመሆን የመንፈስ ቅዱስም ስም የአብ የወልድ ስም ወደመሆን አይፋለስም፤ አይለወጥም" "ኢይፈልስ ስመ አብ ለከዊነ ስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወኢይፈልስ ስመ ወልድ ለከዊነ ስመ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢይፈልስ ስመ መንፈስ ቅዱስ ለኮዊነ ስመ አብ ወወልድ" እንዳለ አግናጥዮስ።

3) <u>የግብር ሦስትነት፡-</u> የአብ ግብሩ ወልድን መውለድ፣ መንፈስ ቅዱስን ማሥረፅ፤ የወልድ ግብሩ ከአብ መወለድ፤ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ከአብ መሥረፅ ነው። አብ ወልድን ወልዷል፣ መንፈስ ቅዱስን አሥርጿል እንጂ እንደ ወልድ አልተወለደም፣ አይወለድም፤ እንደመንፈስ ቅዱስ አልሠረጸም፣ አይሠርጽም። ወልድም ይወለዳል (ተወልዷል) እንጂ አይወልድም፣ አይሠርጽም፣ አያሠርጽምም። መንፈስ ቅዱስም ይሠርጻል እንጂ አይወለድም፣ አያሠርጽም አይወልድም ስለዚህ ሱንትዮስ "ነአምን በአብ በሥርዓት አብና ወለወልድኒ በሥርዓ ተ ወልድና ወለመንፈስ ቅዱስኒ በሥርዓተ ሥርጽና" ብሏል አብ የወልድ አባት ወላዲ የመንፈስ ቅዱስ አሥራጺ ቢሆንም አይቀድማቸውም፤ አይበልጣቸውም። "ኢሀሎ አብ ዘመነ ዘእንበለ ወልድ ወኢሀሎ ወልድ ዘመነ ዘእንበለ መንፈስ ቅዱስ ኢ አሐተሰዓተ ወኢቅጽበተ ዓይን" ብለዋል። አባቶቻችን ከዚህ የቀረውን "አብ ማን ነው?" "ኢየሱስ ማን ነው?" "መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?" የሚሉትን ክፍሎች ይመልከቱ።

ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ።



<u>ጥያቄዎች</u>

1. የሃይማኖት መሠረት እና የሰው ልጅ የሕይወት ጥያቄዎች መልስ ምንድን ነው?
2. ስለእግዚአብሔር መኖር መጻሕፍት ምን ያስተምራሉ? መልሱን በጥቅስ ይግለጹ።
3. ሕልውና ምንድን ነው?
4. ምክንያት የሌለው ህላዌ ማለት ምን ማለት ነው?
5. ሰዎች ለምን ሀልወተ እግዚአብሔርን ይጠራጠራሉ?
6. የእግዚአብሔር መኖር የተገለጸባቸውን መንገዶች ይጥቀሱ ስንት ናቸው?
7. የእግዚአብሔር ባህርይ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው በመዘርዘር ያስረዱ።
8. በአንድነት በሦስትነት በመመለክ በመቀደስ የኖረው እና ያለው ማንነው?
9. አንድነቱ በምን በምን ነው?
10. ሦስትነቱስ በምን ነው?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.